የጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMISION
የውስጥ መገናኛ
INTERNAL OFFICE MEMORANDUM

ቁጥር፡ ጉኦዘ/6.0/4/11

# ለ፡ ጉምሩክ ሥራ አመራር ፕሮጀክት ጽ/ቤት

# ከ፡ ጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ ጽ/ቤት

ዮናስ ተክለወልድ በላይነህ
የጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
ጽ/ቤት ኃላፊ

# ቀን፡ 13/10/2011 ዓ.ም.

ጉዳዩ፡- <u>የመመሪያ ማሻሻያ ሰነድ ስለመላክ፤</u>

በዓለም ገበያ ያለቀለት ቆዳ ፍላጐት በመቀነሱ ምክንያት የቆዳ ኤክስፖርት ንግድ መዳከም ያስከተለውን ከፍተኛ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ብክነት እንዲሁም በቆዳ ፋብሪካዎች በከፊል የተዘጋጀ የቆዳና ሌጦ ክምችት ችግር ለማቃለል በመመሪያው የተወሰነው የታክስ ማስከፈያ ምጣኔ እንዲሻሻል የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ ከግንቦት 21 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ መመሪያው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/343 በቀን 19/9/2011 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን ከጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር በቁጥር 4/540/11 በቀን 11/10/2011 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ገልፀውልናል፡፡

ስለሆነም የተደረገው ማሻሻያ በጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርዓት እንዲካተት እያሳሰብን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የላከው የመመሪያው ማሻሻያ ሰነድ ከዚህ የውስጥ ማስታወሻ ጋር 4 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

<u>እንዲያውቁት/</u>

> ለታሪፍ ምደባና የስሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
> <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

መመሪያ ቁጥር 57/2011

## ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈለውን ታክስ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ገበያ ያለቀለት ቆዳ ፍላጐት በመቀነሱ ምክንያት በቆዳ ዘርፍ የሚታየው የኤክስፖርት ንግድ መዳከም ከፍተኛ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ብክነት እንዲሁም በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ክምችት ያስከተለ በመሆኑ፣

ይህንን ችግር ለማቃለል ወደውጭ በሚላክ በጥሬና በከፊል በተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን የታክስ ማስከፈያ መጣኔዎች ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል በወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 4 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 57/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ማሻሻያ

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 30/2004 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

የመመሪያው አንቀጽ 4 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 4 ተተክቷል።

"4. ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

ሀ) ጥሬ ቆዳና ሌጦ የዋጋው 150%
ለ) ዌትብሉ የበሬ ቆዳ የዋጋው 50%
ሐ) ፒክልድ የበግ ሌጦ የዋጋው 50%
መ) ዌትብሉ የፍየል ሌጦ የዋጋው 50%
ሠ) ክረስት የበሬ ቆዳ የዋጋው 0%

አህመድ ሽዴ
ሚኒስትር

ረ) ክረስት የበግ ሌጦ የዋጋው 0%
ሰ) ክረስት የፍየል ሌጦ የዋጋው 0%

3. <u>*መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*</u>

ይህ መመሪያ ከግንቦት 21 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

ለውጭ ገበያ ቆዳና ሌጦ.Boc/GT